የሰበር መ/ቁ 49797

መጋቢት 30 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሀኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አልሀበሽ ሹገር ሚልስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር -

ተወካይ አቶ ተካልኝ መለሰ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ተገኔ ገ/ሃዋርያት - ከጠበቃ አብዱራህማን መሐመድ ጋር ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 54585 ሀምሌ 17 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የከፍተኛው ፍርድ ቤት ጥቅምት 2 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ስላመለከተ ነው፡፡

ክርክሩ የታየው በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ በከሳሽነት ቀርቦ በወር ብር 10,000(አስር ሺህ ብር) እየተከፈለው በአመልካች ድርጅት ሢሠራ እንደነበር ገልፆ አመልካች መጋቢት 11 ቀን 2001 ዓ.ም ከሥራ አላግባብ ያሰናበተኝ ስለሆነ ወደ ሥራ እንድመለስ ወይም የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፍሉኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ ተጠሪን ያሰናበተው መኪናና ሹፌር ተመድቦለት እየተገለገለ እያለ ታህሣሥ 30 ቀን 2001 ዓ.ም የድርጅቱን መኪና ቁልፍ ከሹፌሩ በመረከብ በማሽከርከር ላይ እያሉ የድርጅቱን መኪና በማጋጨት ጉዳት አድርሷል፡፡ ስለዚህ ስንብቱ ህጉን መሠረት ያደረገ በመሆኑ የከሳሽ (ተጠሪ) ጥያቄ ተገቢነት የለውም የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ለመደገፍ ያቀረቡትን ማስረጃ ሣይሰማና ሣይመረምር አመልካች ተጠሪን ያሰናበተው የሥራ ስንብት ደብዳቤ ፅፎ ሣይሆን በቃል በመሆኑ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው በማለት አመልካች ለተጠሪ የአምስት ወር ደመወዝ በመክፈል ወደሥራው እንዲመልሰው በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ለዚህ ችሎት የቀረበው የሰበር አቤቱታ ተጠሪ ከሥራ የተባረረው በጥፋቱ ነው፡፡ ተጠሪን የጥፋቱ ተጠቃሚ የሚያደርግ ውሣኔ መሠጠቱ የህግ ስህተት ያለበት ውሣኔ ነው፡፡ ተጠሪ ከሥራ የተባረረው የሥራ ውሉ ሊጠናቀቅ አንድ ወር ሲቀረው በመሆኑ የአምስት ወር ደመወዝ ከፍላችሁ ወደሥራ መልሱ በማለት የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ችሎት ማስረጃችንን በመቀበል ውሣኔ ይሰጥልን በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ እኔ የተቀጠርኩት ላልተወሰነ የሥራ ጊዜ ነው፡፡ ስለዚህ አመልካች የሥራ ውሉ ሊጠናቀቅ አንድ ወር ሲቀረው ነው ያሰናበትኩት በማለት ያቀረበው ክርክር የህግ መሠረት የለውም፡፡ አመልካች በህጉ የተመለከተውን ሥርዓት ሣያሟላ ከሥራ ማሰናበቱ ህገ-ወጥ ስለሚያደርገው የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ አቅርቧል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የቀረበው ክርክርና በሰበር ያቀረበው የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ተጠሪን ከሥራ ያሰናበተው በፅሑፍ ሣይሆን በቃል መሆኑ ብቻ

ስንብቱ ህገ-ወጥ መሆኑን ያሣያል በማለት አመልካች ተጠሪን የአምስት ወር ደመወዝ ከፍሎ እንዲመልስ በማለት የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? በሚለው ጭብጥ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ለዚህ ጭብጥ እልባት ለመስጠት በመጀመሪያ የሥር ፍርድ ቤት አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩበትን መሠረታዊ ጭብጥ በመለየትና በመመሥረት ለክርክሩ እልባት የሰጠ መሆኑን መመርመር ያስፈልጋል፡፡ አንድ ጭብጥ የሚመሰርተው ከሳሽ በክሱ የገለፀውን ተከሳሹ ክዶ የሚከራከር ሲሆን እንደሆነ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 247 ተደንግጓል፡፡ ተጠሪ አመልካች አላግባብ ከሥራ ያሰናበተው መሆኑን ገልፆ ክስ ያቀረበ ሲሆን አመልካችም ተጠሪን ከሥራ አላሰናበትኩትም የሚል ክርክር አላቀረበም፡፡ አመልካች ተጠሪን ከሥራ አሰናብቸዋለሁ በማለት በግልፅ መልስ ሰጥቷል፡፡ ስለሆነም አመልካች ከተጠሪ ጋር ያለውን የሥራ ውል ማቋረጡ ግራቀኙ የሚተማመኑበት ነጥብ በመሆኑ ስንብቱ በፅሑፍ ነው ወይስ በቃል የሚል ማጣሪያ ማድረግ የሚያስፈልገው አይደለም፡፡ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 27 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት አሠሪው ለሠራተኛው የሥራ ውሉ ያቋረጠበትን ምክንያት በፅሑፍ አለመግለፁ ብቻውን ስንብቱን ህገ ወጥ የሚያደርግ አይደለም፡፡ አሠሪው ይህንን ሣይፈፅም ቢቀርና በፅሑፍ ሣይሆን በቃል ወይም በድርጊት የሥራ ውሉን ቢያቋርጥ የሥራ ውሉን ለማቋረጥ የሚያበቃ ምክንያት ያለው መሆኑን ከመከራከርና ማስረጃ ከማቅረብ የሚገድብ አይደለም፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ሣይሰማና ግራቀኙ የሚከራከሩበትን ጭብጥ ሣይመሰርት ስንብቱ በፅሑፍ ያልተደረገ በመሆኑ ብቻ አመልካች ከተጠሪ ጋር ያለውን የሥራ ውል አላግባብ አሰናብቷል በማለት የሰጠው የሕግ ትርጉምና ውሣኔ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በአንድ ጉዳይ ጭብጥ የሚመሠረተው ከሳሽ ያቀረበውን ክስና ማስረጃ ተከሳሽ የሚሰጠውን የመከላከያ መልስና ማስረጃና ፍርድ ቤቱ በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 241 መሠረት በሚያደርገው የቃል ምርመራ የተሰጠ መልስ መሠረት በማድረግ መሆን እንዳለበት የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 248 ይደነግጋል፡፡ በዚህ ጉዳይ አመልካች ከተጠሪ ጋር ያለውን የሥራ ውል ማቋረጡ አከራካሪ ጭብጥ አይደለም፡፡ አከራካሪው ጭብጥ አመልካች በድርጅቱ መኪና ላይ ጉዳት በማድረሡና ያለማስጠንቀቂያ የሥራ ውሉን ለማሰናበት የሚችል ጥፋት በመፈፀሙ ስንብቱ ህጋዊ ነው የሚል ክርክር ያቀረበና ይህንን ለማስረዳት የማስረጃ ዝርዝር መግለጫ ያቀረበ መሆኑን ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤት አመልካችና ተጠሪ የሚካካዱበትን ይህንን ጭብጥ በመመሥረትና በማስረጃ በማጣራት ውሳኔ መስጠት ሲገባው የሥራ ስንብቱ በቃል የተደረገ መሆኑ ብቻውን ስንብቱ ህገ-ወጥ መሆኑን ያሣያል በማለት የሰጠውን ውሣኔ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ሣያርም እንዳለ ማፅናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት አመልካች ተጠሪን ከሥራ ያሰናበተው ሠራተኛው(ተጠሪ) ከሥራ ሊያሰናብት የሚችል ጥፋት በመፈፀሙ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥና ሌሎች ነጥቦች ለማስረዳት በግራ ቀኙ በኩል ያቀረበውን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ውሣኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343(1) መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት የወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምፅ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ